# LES ENSEIGNANTS DE LA SECTION D'AMHARIQUE

*De 1898 à aujourd'hui*

# የማርኛ ክፍለ ትምህርት መምህራን

ከ፲፰፻፺፩ ዓ.ም. እስከ ዛሬ


Compilé par
Yaël Rouillard, Natalia
Danilova et Noam Rouillard

avec le soutien de
Delombera Negga, Margaux
Herman et Ronny Meyer



ዋና ሰብሳቢዎች፦
ያዔል ሩያር፣ ናታልያ ዳኒሎቫና ኖዓም
ሩያር

አጋዥ፦
ድልወንበራ ነጋ፣ ማርጎ ኤርማንና
ሮኒ ማየር



Paris, 2024

ፓሪስ፣ ፳፻፲፮ ዓ.ም.

# *De 1898 jusqu'après la Seconde Guerre mondiale*

# ከ፲፰፻፺፩ ዓ.ም. እስከ ኹለተኛው ያለም ጦርነት መጨረሻ

(የተጠቀሱት ዓመታት በሙሉ እንዳውሮጳውያን አቆጣጠር (እአአ) ነው።)



1898–12/1910 **Casimir Mondon-Vidailhet**
**ካዚሚር ሞንዶን ቪዳዬ**
(*1847–†1910)

01–08/1911 **Joseph Blanchart**
**ዠዜፍ ብላንሻር**
(*1866–†?)

11/1911–1950 **Marcel Cohen**
**ማርሴል ኮኼን**
(*1884–†1874)

1937–1939 **Wolf Leslau**
**ዎልፍ ሌስላው**
(*1906–†2006)

**Déborah Lifchitz**
**ዴቦራ ሊፍቾትስ**
(*1907–†1942)

01/1941–1944 **Marcel Griaule**
**ማርሴል ግሪዮል**
(*1889–†1956)

## *Répétiteurs :*

## የቋንቋ አለማማጅ መምህራን፦

1937–1938 **Makbeb Demté**
**መክበብ ዳምጤ**

1938–1939, 1945–1956 **Teklé Gourmou**
**ተክሌ ጉርሙ**

1942–1945 **Taffäsä Habtämikaél**
**ታፈሰ ሀብተ ሚካኤል**

# D'après la Seconde Guerre mondiale à aujourd'hui
# ከኹለተኛ ዓለም ጦርነት በኋላ እስከ ዛሬ

## Enseignants
## አስተማሪዎች

### des langues
### ለቋንቋ

| | |
|---|---|
| 1950–1974 | Joseph Tubiana<br>ዦዜፍ ቱቢያና<br>(*1919–†2006) |
| 1965–1974 | Makonnen Argaw<br>መኰንን አርጋው<br>(*1935–†2015) |
| 1974–2014 | Meaza H. Revol-Tissot<br>መዓዛ ሬቮል ቲሶ |
| 2001 | Delombera Negga<br>ድልወንበራ ነጋ |
| 2017 | Ronny Meyer<br>ሮኒ ማየር |



### de la civilisation
### ለሥልጣኔ

| | |
|---|---|
| 1969–1981 | Michel Perret<br>ሚሼል ፔሬ<br>(*1933–†2019) |
| 1981–1994 | Alain Rouaud<br>አላን ሩዎ |
| 1994–2010 | Alain Gascon<br>አለን ጋስኮን |
| 1995–1997 | Bertrand Hirsch<br>ቤርትራን ኢርሽ |
| 2010–2018 | Benjamin Volff<br>ቤንዥማን ቮልፍ |
| 2018–2022 | Serge Dewel<br>ሴርዥ ዱዌል |
| 2022 | Margaux Herman<br>ማርጎ ኤርማን |

## D'après la Seconde Guerre mondiale à aujourd'hui
## ከኹለተኛ ዓለም ጦርነት በኋላ እስከ ዛሬ

### Répétiteurs et professeurs invités pour les langues éthiosemitiques :
### የኢትዮ-ሴማዊ ቋንቋዎች አለማማጅ መምህራንና የተጋበዙ አስተማሪዎች፦

amharique / ዐማርኛ ፦

1956–1959 Joseph Mokrea
ዮሴፍ መኩሪያ
(*1926–†?)

1959–1965 Berhanu Abebe
ብርሃኑ አበበ
(*1932–†2008)

1965–1977 Abba Jérôme
አባ ዤሮም
(*1881–†1983)

1970–1971 Irdaou Guetahoun
ይርዳው ጌታኹን

1970–1974 Jean-Maurice Le Gal
ዣን ሞሪስ ለ ጋል
(*1938–†2020)

1972–1973 François Enguehard
ፍራንሷ ኤንግሃርድ

1977–1979 Olga Kapeliuk
ዖልጋ ካፔልዩክ

2002–2017 Hayat Omar
ሐያት ኦመር

2017–2019 Hirut Kebbede
ሂሩት ከበደ

2023–2024 Yohannes Beyene
ዮሐንስ በየነ

2021–2023 Fanny Gimenez
ፋኒ ዢመኔዝ

2021–2022 Arthur Danjean
አርቱር ዳንዣን

## D'après la Seconde Guerre mondiale à aujourd’hui
## ከኹለተኛ ዓለም ጦርነት በኋላ እስከ ዛሬ

### Répétiteurs et professeurs invités pour les langues éthiosemitiques :
### የኢትዮ-ሴማዊ ቋንቋዎች አለማማጅ መምህራንና የተጋበዙ አስተማሪዎች፦

**tigrigna / ትግርኛ ፦**

1965–1977 **Abba Jérôme**
**አባ ዤሮም**
(*1881–†1983)

1974–2014 **Meaza H. Revol-Tissot**
**መዓዛ ሬቮል ቲሶ**

1977–1979 **Olga Kapeliuk**
**ዖልጋ ካፔልዩክ**



# D'après la Seconde Guerre mondiale à aujourd'hui
# ከኹለተኛ ዓለም ጦርነት በኋላ እስከ ዛሬ

## Répétiteurs pour les autres langues éthiopiennes :
## የሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አለማማጅ መምህራን፦

### «langues couchitiques d'Éthiopie»
### የኢትዮጵያ ኩሽ ቋንቋዎች ፦

1960-1961 Saïd Gouled
ሰይድ ጕለድ

### somali / ሱማልኛ ፦

1959-1960 Ahmed Diria
አህመድ ድሪያ

1962-1964 Ahmed Diria et Ibrahim Harbi
አህመድ ድሪያ እና ኢብራሂም ሀርቢ

1982-1993 Myriam Barre
ሚርያም ባሬ

### afar / አፋርኛ ፦

1962-1964 Kamil Abdallah
ከሚል አብዱላህ

1967-1971 colonel Édouard Chedeville et
ኮሎኔል ኤዱዋር ቼድቪል እና

1967-1969 Hassan Ali Mohamed
ሀሰን አሊ መሐመድ

1970-1971 Barakat Daoud
በረከት ዳውድ

### oromo / ኦሮምኛ ፦

1964-1966 Haïlé Fida
ኃይሌ ፊዳ

# CASIMIR MONDON-VIDAILHET

Autodidacte, Casimir Mondon-Vidailhet (1847–1910) a commencé à étudier l'amharique dès 1877. Arrivé en Éthiopie en mars 1892, il a joué le rôle de représentant officieux de la France auprès de l'empereur Ménélik II. Mais, il rentre en France à la suite de la nomination d'un représentant officiel en la personne de Léonce Lagarde.

Casimir Mondon-Vidailhet fut le premier enseignant de la langue amharique à l'École des langues orientales. La charge de cours d'amharique, crée en 1898, fut fondée dans le contexte du développement des relations entre la France et l'Éthiopie après la bataille d'Adwa en 1896 où l'Éthiopie venait de battre l'Italie.

Après une dizaine d'années d'enseignement de l'amharique aux Langues O', Mondon-Vidailhet meurt en décembre 1910. Au terme de ces années d'enseignement, 36 étudiants ont été diplômés (soit plus, dans la même période qu'en arménien, en japonais ou en tamoul).

Casimir Mondon-Vidailhet est l'auteur de la première grammaire de langue amharique en français. Il est aussi connu pour la traduction de la chronique de l'empereur Téwodros II.

(*1847–†1910)



# ካዚሚር ሞንዶን ቪዳዬ

ያለ አስተማሪ እራሳቸውን ያስተማሩ ካዚሚር ሞንዶን ቪዳዬ (1847–1910)፥ በ1877 ዐማርኛ ማጥናት ጀመሩ። በመጋቢት ወር 1892 ኢትዮጵያ ሲደርሱ እንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ ዘንድ ይፋዊ ያልኾኑ የፈረንሳይ መንግሥት ተወካይ ኾነው ነበር። ሌኦንስ ላጋርድ በተወካይነት ከተሾሙ በኋላ ግን ካዚሚር ሞንዶን ቪዳዬ ወደ ፈረንሳይ አገር ተመልሰው በምሥራቅ ቋንቋና ሥልጣኔ ሀገራዊ ተቋም (ኢናልኮ) ያማርኛ አስተማሪ ኾኑ።

ካዚሚር ሞንዶን ቪዳዬ፥ በ1898 በኢናልኮ ያማርኛ ክፍለ ትምህርት ሲቋቋም የመጀመሪያው አስተማሪ ነበሩ። ያማርኛ ክፍለ ትምህርትም የተመሠረተው፣ ኢትዮጵያ ጣሊያንን በ1896 ድል ካደረገችበት ከአድዋ ጦርነት በኋላ በፈረንሳይና በኢትዮጵያ መካከል የነበረው ግንኙነት በሚጠናከርበት ወቅት ነበር።

ካዚሚር ሞንዶን ቪዳዬ በኢናልኮ ላሥር ዓመታት ዐማርኛን ካስተማሩ በኋላ በታኅሣሥ ወር 1910 አረፉ። በመምህርነት ዘመናቸው 36 ተማሪዎች ባማርኛ ቋንቋ አስመርቀዋል። ይኸውም፥ ባርመንኛም ኾነ በጃፓንኛ ወይም በታሙል ቋንቋ ከተመረቁት ተማሪዎች በላይ ነበር።

ካዚሚር ሞንዶን ቪዳዬ የመጀመሪያውን ያማርኛ ቋንቋ ሰዋስው በፈረንሳይኛ የደረሱ ናቸው። እንዲሁም የዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስን ዜና መዋዕል በመተርጎም ይታወቃሉ።

# MARCEL COHEN

# ማርሴል ኮኼን

(*1884–†1974)

Diplômé d'abord en arabe maghrébin, Marcel Cohen choisit de se réorienter vers les langues éthiosémitiques et effectue une mission en Éthiopie en 1910–1911. En novembre 1911, il succède à Casimir Mondon-Vidailhet en tant que chargé de cours à l'École nationale des langues orientales vivantes (ENLOV). Agrégé de grammaire, arabisant et initié aux langues sémitiques d'Éthiopie, il enseigne la langue amharique et la civilisation éthiopienne. Marcel Cohen est promu professeur adjoint durant la Première guerre mondiale, puis quand la chaire d'amharique est créée en 1926, il devient professeur titulaire. Il est également directeur d'études à la IVe section de l'École pratique des hautes études (EPHE) où il enseigne le guèze. En 1931, il crée le Groupe linguistique d'études chamito-sémitiques (GLECS), toujours en activité.

De 1937 à 1939, Marcel Cohen est détaché à la Caisse nationale de la recherche scientifique. Il est alors provisoirement remplacé par deux de ses élèves les plus avancés : Wolf Leslau qui enseigne la langue et Déborah Lifchitz qui assure les cours de civilisation. En décembre 1940, Marcel Cohen est révoqué et mis à la retraite en tant que juif.

Après la Libération, il réintègre l'École des Langues O' où il enseigne l'amharique jusqu'en 1950, et l'EPHE où il donne des cours de guèze jusqu'en 1955.





ማርሴል ኮኼን በመጀመሪያ በመግሪቢ አረብኛ ተመረቁ። ከዚያ በኋላ ግን የጥናታቸው ፍላጎት ወደ ኢትዮ-ሴማዊ ቋንቋዎች ስለዞረ ከ1910 እስከ 1911 ወደ ኢትዮጵያ ለመስክ ጥናት ኼዱ። በኅዳር ወር 1911 በዘመናዊ የምሥራቅ ቋንቋ ሀገራዊ ትምህርት ቤት (ENLOV) ያማርኛ አስተማሪ የነበሩትን ካዚሚር ሞንዶን-ቪዳየን በቋንቋ መምህርነት ተክተዋል። የሥነ ልሳንና ያረብኛ ቋንቋ ምሁር ኾነው የኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋዎችን ማጥናት ከጀመሩ በኋላ ያማርኛ ቋንቋና የኢትዮጵያን ስልጣኔ ያስተምሩ ነበር። ማርሴል ኮኼን ባንደኛው ያለም አቀፍ ጦርነት ወቅት በረዳት ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ተሹመው፥ በ1926 ላማርኛ ክፍለ ትምህርት የሊቀ መንበር ቦታ ሲፈጠር ሙሉ ፕሮፌሰር ኾነው ተሾሙ። እንደዚሁም፥ የከፍተኛ ጥናት ተግባራዊ ተቋም (EPHE) በተባለው ዩኒቨርሲቲ የጥናት ዳይሬክተር ኾነው የግእዝ ቋንቋን አስተምረዋል። በ1931 የኩሽና የሴም ቋንቋዎች የሥነ ልሳን ጥናት ቡድን (GLECS) አቋቋሙ። ይህ ቡድን አሁንም ሥራውን እንደቀጠለ ነው።

ከ1937 እስከ 1939 ድረስ በሀገራዊ የሳይንስ ምርምር ማዕከል በሚሠሩበት ገዜ፥ በኢናልኮ  በኹለቱ በጣም የላቁ ተማሪዎቻቸው ተተኩ። ቋንቋውን ያስተማሩት ቮልፍ ሌስላው ሲኾኑ ዴቦራ ሊፍቺትስ ደግሞ የስልጣኔ ትምህርት ይሰጡ ነበር። ማርሴል ኮኼን አይሁድ ስለነበሩ በ1940 በታኅሣሥ ወር ከሥራቸው ታግደው ወደ ጡረታ እንዲወጡ ተደርጓል።

ጦርነት አልቆ ነጻነት ከተመለሰ በኋላ ማርሴል ኮኼን ወደ ኢናልኮ ተመልሰው እስከ 1950 አማርኛን ሲያስተምሩና በከፍተኛ ጥናት ተግባራዊ ተቋም (EPHE) ደግሞ የግእዝ ትምህርት እስከ 1955 ድረስ ሲሰጡ ቈይተዋል።

# MARCEL GRIAULE

# ማርሴል ግሪዮል

(*1889–†1956)





Élève de Marcel Mauss et de Marcel Cohen, détenteur de la Croix du combattant de la Première guerre mondiale et de la médaille de la Marne, Marcel Griaule effectue sa première mission en Éthiopie en 1928-1929 pour ensuite entreprendre sa grande et célèbre mission Dakar-Djibouti (mai 1931- février 1933). En 1935-1936, il fournit son aide à la délégation éthiopienne pour rédiger la réponse à un mémoire présenté par l'Italie à la Société des Nations et collabore par la suite à la rédaction du discours de l'empereur Haïlé Sélassié que ce dernier prononcera devant l'Assemblée Générale de la Société des Nations le 30 juin 1936. Entre 1940 et la Libération, Marcel Griaule remplace Marcel Cohen en tant que chargé d'enseignement d'amharique à Langues O'. En 1943, il devient directeur de la première chaire d'ethnologie à la Sorbonne, et par la suite, il se consacrera à l'étude de l'Afrique de l'Ouest.

የማርሴል ሞስና የማርሴል ኮኼን ተማሪ የነበሩና ባንደኛው ያለም ጦርነት ያርበኝነት ተጋድሎ ኒሻንና የማርን ክፍለ ሀገር ሜዳላይ የተሰጣቸው ማርሴል ግሪዮል፥ ከ1928 እስከ 1929 ድረስ ለመጀመሪያ ጊዜ ለጥናትና ምርምር ወደ ኢትዮጵያ ኼዱ። ከዚያም ከግንቦት 1931 እስከ የካቲት 1933 ከዳካር እስከ ጅቡቲ ተብሎ የታወቀውን ዋና ጥናታዊ ተልእኮ መርተዋል። በ1935-1936 ደግሞ፥ ጣሊያን ላለም መንግሥታት ማኅበር ላቀረበቸው የቅሬታ ማስታወሻ መልሱን በማዘጋጀት ረገድ ለኢትዮጵያ ልኡካን ቡድን ርዳታቸውን አበርክተዋል። ሰኔ፣ 30 ቀን፣ 1936 ባለም መንግሥታት ማኅበር ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ያቀረቡትን ያፄ ኃይለ ሥላሴን ንግግር በመጻፍ ተባብረዋል። ከ1940 ጀምሮ እስከ 1945 ድረስ ማርሴል ግሪዮል በምሥራቅ ቋንቋና ሥልጣኔ ሀገራዊ ተቋም (ኢናልኮ) ማርሴል ኮኼንን ተክተው ያማርኛ ክፍለ ትምህርት ኀላፊ ነበሩ። በ1943 በሶርቦን ዩኒቨርሲቲ የሥነ ሰብእ ክፍለ ትምህርት የመጀመሪያው ሊቀ መንበር ከኾኑ በኋላ ጥናታቸው ያተኰረው በምዕራብ አፍሪቃ ላይ ነበር።

# TEKLÉ GOURMOU

(*1912–†?)

Teklé Gourmou est né en 1912 aux environs d'Asmara en Erythrée. Il étudie le tigrigna, l'italien et l'amharique et obtient une bourse du gouvernement éthiopien pour aller étudier au lycée français d'Alexandrie où il obtient son baccalauréat.

En 1932, il intègre l'École des ingénieurs des PTT de Vanves dont il sortira sous-ingénieur radio-électricien. En 1935, lors de l'invasion italienne en Éthiopie, il rejoint les troupes impériales et devient chargé de la direction générale des télécommunications pour le Gojdam. De retour en France, Teklé Gourmou devient répétiteur d'amharique de 1938 à 1939. Ayant été naturalisé Français, il est mobilisé lors de la Seconde Guerre mondiale. Après la guerre, il reprend son enseignement à Langues O', en charge de cours (1945-1949), puis comme répétiteur (1949–1956).

En avril 1956, malgré ses états de service, la qualité de son enseignement et le soutien de l'École, Teklé Gourmou est renvoyé des Langues O' à la suite de deux poèmes de contestation qu'il rédige, «Témoignages et conseils» (partie 1 et 2). Dans le premier, il plaide pour l'unité du peuple éthiopien, tandis que dans le second il critique directement le gouvernement éthiopien qui demande alors son renvoi.



# ተክሌ ጕርሙ

ተክሌ ጕርሙ በ1912 ኤርትራ ውስጥ አስመራ አካባቢ ተወለዱ። ትግርኛ ጣሊያንኛና ዐማርኛ ከተማሩ በኋላ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት አሌክሳንድሪያ እሚገኘው የፈረንሳይ ትምህርት ቤት ላካቸው።

ባካሎሬያቸውን አግኝተው፣ እፈረንሳይ አገር ቫንብ ከሚገኘው የፖስታና ቴሌኮሙኒኬሽን የመሐንዲስ ትምህርት ቤት ተመርቀው፣ በ1932 የራዲዮ ኤሌክትሪክ ንዑስ መሐንዲስ ኾኑ። በ1935 ጣሊያን ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት በንጉሠ ነገሥቱ የጦር ኀይል ሥር የጎጃም ቴሌኮሙኒኬሽን ዋና ኀላፊ ኾኑ። ከዚያ በኋላ ወደ ፈረንሳይ ተመልሰው በኢናልኮ ከ1938 እስከ 1939 ድረስ ያማርኛ ቋንቋ አስተማሪ በመሆን አገለገሉ። የፈረንሳይ ዜግነት ካገኙ በኋላ በኹለተኛው ዓለም ጦርነት ለውጊያ ተላኩ። ከጦርነቱ በኋላ ከ1945 እስከ 1956 እንደገና ባማርኛ አስተማሪነት አገለገሉ።

በ1956 ባገልግሎታቸውና ባስተማሪነታቸው የተመሰገኑ ስለኾኑ ኀላፊዎቻቸው ቢደግፏቸውም፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ጠይቆ ተክሌ ጕርሙ ከኢናልኮ ሥራቸው ተሰናብተዋል። ይኸውም «ምስክርነት እና ምክር» (ከፍል 1 እና 2) የተባሉትን ኹለት ግጥሞች ስለገጠሙና በመጀመርያው ግጥም ለሕዝብ አንድነት ሲማጸኑ በኹለተኛው ግጥም ግን የኢትዮጵያ መንግሥትን በቀጥታ ስለተቹና ስለወቀሱ ነው።

# JOSEPH TUBIANA

Joseph Tubiana est né en 1919 à Alger. Élève de Marcel Cohen, il apprend l'amharique à l'École Nationale des Langues Orientales Vivantes (ENLOV), le guèze à l'Institut catholique avec S. Grébaut et à l'EPHE avec M. Cohen.

Diplômé d'ethnologie en 1946 et d'amharique en 1948, il entreprend un voyage de recherche ethnographique et linguistique dans le nord de l'Éthiopie de 1949 à 1950. Sur place, il étudie l'amharique et le guèze, ainsi que les langues agaw, et travaille sur les Kemant et les Falacha. De retour en France, il est chargé de cours d'amharique en 1950, puis professeur titulaire de la chaire d'amharique en 1957. En 1974, après 25 ans d'enseignement à l'INaLCO, il réintègre le CNRS qui lui demande de créer un centre de recherche sur l'Afrique orientale à Sophia Antipolis. Il prend sa retraite en 1985 et meurt en 2006 à Paris.

Dans le cadre de son enseignement, Joseph Tubiana procède à des innovations pédagogiques par la mutualisation des cours de civilisation à différents niveaux. Ces cours généraux sont divisés en trois parties : histoire, ethnologie et géographie. Il organise également des conférences sur d'autres langues éthiopiennes, particulièrement sur le somali (avec Ahmed Diria et Ibrahim Harbi entre 1959-1964), les « langues couchitiques » d'Éthiopie (avec Saïd Gouled en 1960-1961), l'afar (avec Kamil Abdallah entre 1962-1964, le colonel Édouard Chedeville entre 1968-1971) et l'oromo (avec Haïlé Fida en 1964-1965).

En 1965, il fait venir Abba Jérôme en France où il enseigne la littérature amharique et le tigrigna à L'INaLCO jusqu'en 1977.

(*1919-†2006)





© Famille Tubiana

# ዦዜፍ ቱቢያና

በ1919 ዦዜፍ ቱቢያና በአልዤር ከተማ ተወለዱ። በ1945 ወደ ትምህርታቸው እንደገና ተመልሰው፥ የማርሴል ኮኼን ተማሪ ኾነው በዘመናዊ የምሥራቅ ቋንቋ ሀገራዊ ትምህርት ቤት (ENLOV) ዐማርኛ ተማሩ። በካቶሊክ ተቋምና በከፍተኛ ጥናት ተግባራዊ ተቋም (EPHE) ደግሞ ግእዝ ተማሩ።

በ1946 በሥነ ሰብዕ ከዚያም በ1948 ባማርኛ ተመርቀው፥ ከ1949 እስከ 1950 ድረስ የሥነ ሰብዕና የቋንቋ ምርምር ለማድረግ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ኼዱ። እዚያም ዐማርኛ፣ ግእዝና የአገው ቋንቋዎችንና በተጨማሪም ስለቅማንትና ስለፈላሻ ሕዝቦች አጥንተዋል። ወደ ፈረንሳይ አገር ከተመለሱ በኋላም በምሥራቅ ቋንቋና ሥልጣኔ ሀገራዊ ተቋም (ኢናልኮ) ባማርኛ መምህርነት በ1950 ተቀጥረው በ1957 ያማርኛ ክፍል ትምህርት ኀላፊ ኾነው በሙሉ ፕሮፌሰርነት ተሾሙ። በ1974 ለ25 ዓመታት ያኽል ካስተማሩ በኋላ፥ ወደ ሀገራዊ የሳይንስ ምርምር ማዕከል (CNRS) ተመለሱ። ያን ጊዜ ማዕከሉ በጠየቃቸው መሠረት ሶፊያ አንቲፖሊስ በሚባለው ከተማ የምሥራቅ አፍሪቃ የምርምር ማዕከል አቋቋሙ። በ1985 ጡረታ ወጥተው በ2006 በፓሪስ ከተማ አረፉ።

ዦዜፍ ቱቢያና ባስተማሪነት ወቅታቸው አንዳንድ የትምህርት አሰጣጥ ማሻሻዮች አመጡ። ይኸውም፥ በተለያየ ደረጃ (ዓመት) የሚማሩ ተማሪዎች አንድ ላይ የጋራ የሥልጣኔ ትምህርት እንዲከታተሉ አደረጉ። ኹሉን ያካተተ የነበረውን የሥልጣኔ ትምህርትም በሦስት ራሳቸውን የቻሉ የትምህርት ዓይነቶች ተከፋፍሎ በታሪክ፣ በሥነ ሰብዕና በሥነ መልክዓ ምድር ተመደበ። በተጨማሪ ለተወሰኑ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ትምህርታዊ ስብሰባ በየጊዜው አዘጋጅተዋል። እነዚህ ስብሰባዎች የሚከተሉትን ቋንቋዎች ያጠቃልላሉ፦ ሱማልኛ ከአህመድ ዲሪያና ከኢብራሂም ሃርቢ ጋራ (1959-1964)፣ የኢትዮጵያ ኩሽ ቋንቋዎች ከሰይድ ጉሌድ (1960-1961)፣ አፋርኛ በመጀመሪያ ከካሚል አብደላህ ጋራ (1962-1964)፣ ከዚያም ከኮሎኔል ኤዷር ቼድቪል ጋራ (1968-1971)፣ ኦሮምኛ ከኀይሌ ፊዳ ጋራ (1964-1965)። በ1965ዦዜፍ ቱቢያና አባ ዤሮምን እፈረንሳይ አገር አስመጥተዋቸው በኢናልኮ ያማርኛና የትግርኛ ሥነ ጽሑፍ አስተማሪ ኾነው እስከ 1977 ድረስ ሠርተዋል።

# MAKONNEN ARGAW

# መኰንን አርጋው

(*1935–†2015)



Makonnen Argaw est né en 1935 dans une famille catholique du Choa à Metcha, près d'Addis Abeba. Il fréquente l'école traditionnelle. Il commence par l'apprentissage de la langue guèze, avant d'entrer à l'Alliance française puis au Lycée franco-éthiopien Guebré Mariam d'Addis Abeba où il est l'un des élèves pionniers de cette école de renom. Après son baccalauréat, il poursuit ses études à Paris où il arrive en octobre 1960 en tant que boursier de l'École du Louvres où il étudie l'archéologie chrétienne et la muséologie et se forme au métier de conservateur.

Il entre à Langues O' comme répétiteur d'amharique en 1965 et assure cette fonction jusqu'en 1974. Pendant ce temps, il prépare son doctorat en philologie éthiopienne sous la direction de Maxime Rodinson (thèse intitulée Matériaux pour l'étude de la prononciation traditionnelle du guèze, Paris III, 1973). Diplômé de l'École Pratique des Hautes Études (EPHE) IVe section en Études orientales, il publie en 1984 son Lexique guèze-amharique des formes verbales (Paris).

Aux Langues O', il était maître-assistant associé (1974-1981), puis stagiaire (1981-82) et titulaire en 1982. En janvier 1988, Makonnen Argaw devient maître de conférences et remplace Joseph Tubiana qui a intégré le CNRS. Il a pris sa retraite en septembre 2001.

አቶ መኰንን አርጋው በ1935 ሸዋ ክፍለ ሀገር፣ አዲስ አበባ አቅራቢያ በሚገኘው መጫ በሚባለው ቦታ ተወለዱ። እናትና አባታቸው የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ነበሩ። እባህላዊ ትምህርት ቤት የግእዝ ቋንቋ ከተማሩ በኋላ፥ ባዲስ አበባ መጥተው መጀመሪያ አሊያንስ ፍራንሴዝ ከዚያም ሊሴ ገብረ ማርያም እሚባለው የፈረንሳይ ትምህርት ቤት ገቡ። የዚህ ታዋቂ ትምህርት ቤት ፈር ቀዳጅ ተማሪዎች አንዱ ነበሩ። ከኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከተመረቁ በኋላ ትምህርታቸውን ለመቀጠል የነጻ ትምህርት ዕድል (እስኮለርሽፕ) አግኝተው ወደ ፓሪስ  በጥቅምት ወር 1960 ኼዱ። እዚያ የተቀበሩ የክርስቲያን ቅርሶች (የክረስቲያን አርኪዎሎጂ) እና የቤተ መዘክር (ሙዚዮሎጂ) ጥናትን ለመከታተልና በቤተ መዘክር የቅርስ ዕቃ ያዥነት ለመሰልጠን ሉቭ ር እሚባለው የትምህርት ተቋም ገቡ።

በ1965 ኢናልኮ ገብተው እስከ 1974 ድረስ ያማርኛ አለማማጅ መምህር (répétiteur) ኾነው አገለገሉ። በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ፊሎሎጂ የዶክትሬታቸውን ጽሑፍ በማክሲም ሮዳንሶን መሪነት ያዘጋጁ ነበር። የጽሑፉ አርእስት «ለግዕዝ ልማዳዊ መንበብ ጥናት የሚያገለግሉ ምንጮች» ሲኾን በፓሪስ III ዩኒቨርሲቲ በ1973 ተጠናቋል። በከፍተኛ ጥናት ተግባራዊ ተቋም (EPHE) ባለው የምሥራቃውያን ጥናት ክፍለ ትምህርት ተመራቂ ኾነው በፓሪስ ከተማ «የግእዝና ያማርኛ የግሥ እርባታ መዝገበ ቃላት» የተሰኘውን መጽሐፍ በ1984 አሳተሙ።

በኢናልኮ ዩኒቨርሲቲ፣ እንደ ተባባሪ ረዳት መምህር (maître-assistant associé) ከ1974 እስከ 1981 ሠርተው ከዚያም በተለማማጅ ረዳት መምህርነት (maître-assistant stagiaire) ከ1981 እስከ 1982 እና በቋሚ ረዳት መምህርነት (maître-assistant titulaire) ከ1982 ጀምሮ አገልግለዋል። በጥር ወር 1988 ተባባሪ ፕሮፌሰር (MCF) ኾኑ። ዡዜፍ ቱቢያና እሀገራዊ የሳይንስ ምርምር ማዕከል ሲገቡ አቶ መኰንን አርጋው ተኳቸው። በ2001 ጡረታ ወጡ።

# MICHEL PERRET

Historien, diplômé d'études supérieures d'histoire à l'université de Lyon, Michel Perret débute comme professeur d'histoire géographie dans l'enseignement secondaire près de Paris. Élève et diplômé de l'École nationale des langues orientales vivantes (ENLOV) pour la langue amharique en 1968, il devient enseignant chercheur sur l'histoire d'Éthiopie et de l'Afrique orientale durant vingt-cinq années aux Langues O', INALCO. En 1989, il obtient un doctorat de troisième cycle en Études africaines avec une thèse intitulée *L'histoire de l'Éthiopie vue du Tigré ... et autres lieux*, publiée en 2013 à l'Harmattan dans la collection Peiresc.

Pendant de nombreuses années, il assure le secrétariat de l'Association pour la recherche scientifique en Afrique de l'Est (ARESÆ) fondée, comme la collection Peiresc, par Joseph Tubiana dont il fût l'élève.

En 1993, il est nommé Président de la Commission du Bicentenaire de l'École des langues orientales (fondée en 1795). Il coordonne, à cette occasion, le financement et la réalisation du livre *Cuisines d'Orient et d'ailleurs, traditions culinaires des peuples du monde* aux éditions Glénat, en 1995, qui marque la célébration du Bicentenaire. Il a été également président de l'Association des anciens élèves et amis des langues orientales (AAEALO) durant de nombreuses années.

(*1933–†2019)






# ሚሼል ፔሬ

ሚሼል ፔሬ ፣ በሊዮን ዩኒቨርሲቲ በታሪክ ተመርቀው ፣ የሥነ መልክዓ ምድርና የታሪክ አስተማሪ ኾነው የጀመሩት አፓሪስ አቅራቢያ በሚገኝ የኹለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው። በዘመናዊ የምሥራቅ ቋንቋ ሀገራዊ ትምህርት ቤት (ENLOV) ተምረው ደግሞ፣ በ1968 ባማርኛ ቋንቋ ተመርቀው በዚያው በኢናልኮ ተቋም ውስጥ 25 ዓመት ያኽል የምሥራቅ አፍሪቃና የኢትዮጵያ ታሪክ አስተማሪና ተመራማሪ ኾነው አገልግለዋል። በ1989 «የኢትዮጵያ ታሪክ ከትግሬና ከሌሎች ቦታዎች አንጻር» የተባለውን የመመረቂያ ጽሑፋቸውን አቅርበው የዶክትሬት ማዕረግ አግኝተዋል። «ፔሬስክ» በተባለው የሀርማታን አሳታሚ ድርጅት የመጽሐፍ ስብስብ ውስጥ የዶክትሬት ጽሑፋቸውን በ2013 አሳትመዋል።

ለብዙ ዓመታት የምሥራቅ አፍሪቃ የሳይንሳዊ ምርምርና ልማት ማኅበር (ARESÆ) ጽሕፈት ቤት ኀላፊ ኾነው መርተዋል። ይህንን ማኅበርም ኾነ የፔሬስክ የመጽሐፍ ስብስብን ያቋቋሙት ፕ/ር ዦዜፍ ቱቢያና ሲኾኑ፣ ሚሼል ፔሬ የሳቸው፡ ተማሪ ነበሩ።

በ1795 ለተመሠረተው የምሥራቅ ቋንቋ ተቋም ኹለት መቶኛ ዓመት የልደት በዓል ዝግጅት ለተቋቋመው ኮሚቴ፣ ሚሼል ፔሬ ሊቀ መንበር ተብለው በ1993 ተሾሙ። ለዚህ ልደት መታሰቢያ ይኾን ዘንድ፣ «የምሥራቅና የሌሎች ሀገሮች የምግብ ዐይነቶች፥ ያለም ሕዝቦች ባህላዊ የምግብ አሠራር» የተሰኘውን መጽሐፍ ባጀቱንና አዘገጃጀቱን አስተባብረው በ1995 በግሌና ማተሚያ ቤት ታትሟል። እንዲሁም ለብዙ ዓመታት «የቀድሞ ተማሪዎች እና የምሥራቅ ቋንቋ ወዳጆች» (AAEALO) ማኅበር ሊቀ መንበር ነበሩ።

# ALAIN ROUAUD

Alain Rouaud débute ses études d'amharique à l'École nationale des Langues orientales vivantes (ENLOV) en 1967. Déjà diplômé d'arabe littéral, il est diplômé une première fois en 1971, il obtient son diplôme avancé d'amharique et de civilisation de l'Afrique orientale en 1980. Il soutient son Doctorat en Études africaines à INaLCO en 1988 et sa thèse est publiée en 1991 sous le titre suivant : Afä-Wärq. *Un intellectuel éthiopien témoin de son temps (1868-1947)*. Paris, Éditions du CNRS.

Alain Rouaud a enseigné à l'INaLCO en tant que chargé de cours de 1981 à 2009. Il a créé et dispensé plusieurs enseignements en histoire culturelle dont l'histoire de la littérature éthiopienne et l'histoire des communautés religieuses en Afrique de l'Est.

Directeur de recherche au CNRS, Alain Rouaud a dirigé plusieurs thèses soutenues à l'INaLCO dont celle de Lukian Prijac, Stéphane Ancel et Jérôme Tubiana.

Alain Rouaud a été le Secrétaire général de l'Association française pour le développement de la recherche scientifique en Afrique de l'Est (ARESÆ). Spécialiste des langues et civilisations de la Corne de l'Afrique et d'Arabie du Sud il a été aussi le directeur de la revue Pount avec un autre éthiopisant, Didier Morin, diplômé d'amharique (1970) et unique diplômé de langue Afar à l'INaLCO.



# አላን ሩዎ

አላን ሩዎ በዘመናዊ የምሥራቅ ቋንቋ ሀገራዊ ትምህርት ቤት (ENLOV) ባረብኛ ተመርቀው ያማርኛ ትምህርታቸውን የጀመሩት በ1967 ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ ባማርኛ የተመረቁት በ1971 ሲኾን በ1980 ደግሞ በላቀ ያማርኛ ቋንቋና በምሥራቅ አፍሪቃ ሥልጣኔ ኹለተኛ ምርቃት አግኝተዋል። በ1988 በምሥራቅ ቋንቋና ሥልጣኔ ሀገራዊ ተቋም (ኢናልኮ) ዶክትሬታቸውን አጠናቀው በ1991 አፈወርቅ፦ ለራሱ ዘመን ምስክር የኾነ ኢትዮጵያዊ (1868-1947) የተሰኘውን የመመረቂያ ጽሑፋቸውን እፓሪስ በሚገኘው ሀገራዊ የሳይንስ ምርምር ማዕከል አሳታሚ ድርጅት አሳተመዋል።

አላን ሩዎ ከ1981 እስከ 2009 በኢናልኮ አስተምረዋል። ትምህርታቸውም ስለኢትዮጵያ ባህል ታሪክ ባዳዲስ አከፋፈል ተዘጋጅቶ የተሰጠ ሲኾን፣ አንዱ ስለኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍ ታሪክ ሌላው ደግሞ በምሥራቅ አፍሪቃ ያሉ የሃይማኖት ማኅበረሰቦች ታሪክ ነበር።

በሀገራዊ የሳይንስ ምርምር ማዕከል (CNRS) የምርምር መሪ ሳሉ፥ አላን ሩዎ የዶክትሬት ተማሪዎች አማካሪ ነበሩ። ከተማሪዎቹም መኻል ሉኪያን ፕሪጃክ፣ ስቴፋን አንሴልና ዤሮም ቱቢያና ይገኙበታል።

አላን ሩዎ የምሥራቅ አፍሪቃ የሳይንሳዊ ምርምርና ልማት ማኅበር (ARESÆ) ዋና ጸሐፊ ነበሩ። ባፍሪቃ ቀንድና በደቡብ አረቢያ ቋንቋዎችና ሥልጣኔዎች ባለሙያነታቸው ከኢትዮጵያ ነክ አጥኒው ከዲድዬ ሞራን ጋራር «ፖውንት» ለሚባለውን መጽሔት ዋና ኀላፊ ነበሩ። ዲድዬ ሞራን ከኢናልኮ ባማርኛና (1970) ባፋርኛ የተመረቁ እሳቸው ብቻ ናቸው።

# ALAIN GASCON

Alain Gascon a étudié l'amharique à l'InaLCO en suivant les cours de Jean-Maurice Legal (1971-73), Joseph Tubiana (1973-74), Mäkonnen Argäw (1971-74) et Michel Perret (1971-74). Diplômé d'amharique en 1974, il a également étudié le somali avec Myriam Barre de 1988 à 1990.

En 1994-1995, Alain Gascon a enseigné à l'INaLCO en remplacement de Michel Perret dont il a assuré les cours au moment où ce dernier travaillait à la rédaction et à la publication du livre consacré au bicentenaire des Langues O'. Puis, en tant que chargé de cours, il a enseigné *l'Histoire de l'Éthiopie et de la Corne de l'Afrique* de 1997 à 2010 et la *Géographie de l'Afrique* de 1997 à 2007.

Professeur des universités à l'Institut français de géopolitique de l'université Paris VIII et professeur honoraire à l'Institut français, Alain Gascon est Président de l'Association pour la promotion de la recherche scientifique en Afrique de l'Est (ARESÆ) et modérateur de son blog. Il a également été membre du comité de rédaction de *Pount* (INaLCO) et des *Cahiers d'études africaines* (EHESS).



# አለን ጋስኮን

አለን ጋስኮን በምሥራቅ ቋንቋና ሥልጣኔ ሀገራዊ ተቋም (ኢናልኮ) የዣን ሞሪስ ለ ጋል (1971-73)፣ የዥዜፍ ቱቢያና (1973-74)፣ የመኰንን አርጋው (1971-74) እና የሚሼል ፔሬ (1971-74) ተማሪ ኾነው ዐማርኛን አጥንተዋል። በ1974 ባማርኛ ተመርቀው ከ1988 እስከ 1990 ሱማልኛን ከሚርያም ባሬ ጋር ተምረዋል።

በ1994-1995 ሚሼል ፔሬ የምሥራቅ ቋንቋና ሥልጣኔ ሀገራዊ ተቋም ኹለት መቶኛ ዓመት መታሰቢያ መጽሐፍ በሚያዘጋጁበትና በሚያሳትሙበት ወቅት፥ አለን ጋስኮን ተክተዋቸው በኢናልኮ ትምህርታቸውን ይሰጡላቸው ነበር። በመቀጠልም በመምህርነት ከ1997 እስከ 2010 የኢትዮጵያና የአፍሪቃ ቀንድን ታሪክ ከዚያም ከ1997 እስከ 2007 የአፍሪቃን ሥነ መልክዐ ምድር አስተምረዋል።

በፓሪስ VIII ዩኒቨርሲቲ ሥር በሚገኘው የፈረንሳይ ፖሊቲካዊ የመልክዐ ምድር ተቋም ሙሉ ፕሮፌሰርና በፈረንሣይ ሀገራዊ ተቋም (Institut français) የክብር ፕሮፌሰር የኾኑት አለን ጋስኮን የምሥራቅ አፍሪቃ የሳይንሳዊ ምርምርና ልማት ማኅበር (ARESÆ) ሊቀ መንበር ናቸው። የማኅበሩም በይነመረብ ጦማር (ብሎግ) አወያይም ናቸው። በተጨማሪ «ፑንት» የሚባለው የኢናልኮ መጽሔት የድርሰት ኮሚቴና የ«ያፍሪቃ የጥናት መዝገብ» የተሰኘው የማኅበራዊ ሳይንስ ከፍተኛ ተቋም (EHESS) መጽሔት ያርትዖት ኮሚቴ አባል ነበሩ።

# BERHANOU ABEBE

# ብርሃኑ አበበ

(*1932–†2008)

Berhanou Abebe est né en 1932 à Addis-Abeba dans une famille catholique. Il fréquente l'école traditionnelle, puis les cours de l'Alliance française et ceux du lycée franco-éthiopien Guebre Mariam à Addis Abeba. Après son baccalauréat, il poursuit ses études de Droit à Paris.

De 1959 à 1965, à la suite de Joseph Mokrea, il est répétiteur d'amharique et prépare son doctorat de 3e cycle d'ethnologie juridique à Langues O' sous la direction de Joseph Tubiana.

Après la soutenance de sa thèse en 1965 il rentre en Éthiopie et occupe des postes importants dans la fonction publique. Entre autres, il était directeur de la Fondation du Prix Haylä Sellasé, directeur adjoint du Chemin de fer franco-éthiopien et professeur associé d'histoire à l'Université d'Addis Abeba.



ብርሃኑ አበበ በ1932 አዲስ አበባ ተወለዱ። ወላጆቻቸው የካቶሊክ እምነት ተከታዮች ነበሩ። ትምህርታቸውን የጀመሩት በባህላዊ ትምህርት ቤት ሲሆን አዲስ አበባ በሚገኙት አሊያንስ ፍራንሴዝና ሊሴ ገብረ ማርያም በሚባለው የፈረንሳይ ትምህርት ቤት ቀጥለዋል። የኹለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ጨርሰው ከተመረቁ በኋላ በፓሪስ ዩኒቨርሲቲ ሕግ ተማሩ።

ከ1959 እስከ 1965 ከዮሴፍ መኩሪያ ቀጥለው ያማርኛ አለማማጅ መምህር (répétiteur) ሲኾኑ በኢናልኮ ዩኒቨርሲቲ በሥነ-ሕግ የዶክትሬት ዲግሪ የመመረቂያ ጽሑፋቸውን በፕ/ር ዦዜፍ ቱቢያና መሪነት አዘጋጁ።

በ1965 የመመረቂያ ጽሑፋቸውን ከጨረሱ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በመንግሥት ሥራና በተለያዩ ከፍተኛ ቦታዎች አገልግለዋል። ለምሳሌ ያኽል፤ የኃይለ ሥላሴ ሽልማት ድርጅት ዳይሬክተር፤ የፍራንኮ-ኢትዮጵያ ምድር ባቡር ድርጅት ምክትል ዳይሬክተርና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ተባባሪ ፕሮፌሰር ነበሩ።

# ABBA JÉRÔME

## Gäbrä Mädhen Gäbrä Musé

(*1865-†1977)

Abba Jérôme, de son vrai nom Gäbrä Mädhen Gäbrä Musé, est né à Säraé (Érythrée) autour de 1880. Il a commencé ses études à Massaoua puis à Kärän auprès des lazaristes français. Ces derniers lui donneront le nom de Jérôme. Suite à l'expulsion des lazaristes, il étudie chez les capucins à Kärän puis à Asmara. Il complète sa formation en tigrigna (langue maternelle) mais étudie également l'amharique, le latin, le guèze, le français, l'italien et les sciences religieuses. Autour de 1900 il est ordonné prêtre séculier de rites éthiopien et deviendra "Abba Jérôme" (père Jérôme). Il enseigne tout en travaillant à l'imprimerie des Capucins à Asmara. Vers 1918, il rompt avec les Capucins et quitte le clergé et l'Érythrée pour l'Éthiopie.

En Éthiopie, il entre alors au service de l'empereur Haylä Sellasé. Il appartient à la Municipalité d'Addis Abeba et remplit plusieurs missions en Europe. En plus, il apporta une aide constante à tous les éthiopisants (M. Cohen, E. Cerulli, M. Griaule, S. Strelcyn, J. Tubiana, etc.), soit lors de leurs passages en Éthiopie, soit lorsque lui-même se rendait en Europe. Il fut délégué du gouvernement éthiopien auprès de la Mission Dakar Djibouti (1931-1933). En 1941, après l'occupation italienne, sa participation à la résistance clandestine à l'occupant étant reconnue, il fut nommé conservateur des manuscrits de la Bibliothèque nationale d'Addis Abeba.

Après sa retraite en 1965 et l'appui de Joseph Tubiana, il viendra à Paris et enseignera aux Langues O' (c'est-à-dire l'Inalco) la littérature amharique et tigrinya jusqu'en 1977.



# አባ ዤሮም

## ገብረ መድኅን ገብረ ሙሴ

ቤተሰባቸው ያወጣላቸው ስም ገብረ መድኅን ገብረ ሙሴ ሲኾን፥ አባ ዤሮም በመባል የሚታወቁት ሊቅ በ1880 አካባቢ ኤርትራ ውስጥ ሰራየ በሚባለው አገር ተወለዱ። መጀመሪያ በምጽዋዕ ቀጥሎ በከረን እፈረንሳውያን የላዛሪስት ሰባኪዎች ዘንድ ትምህርታቸውን መማር ጀመሩ። ያንን ጊዜ ዤሮም የተባለውን ስም አወጡላቸው። የላዛሪስት ሰባኪዎች ካገሩ ስለተባረሩ፥ ትምህርታቸውን እካፑቺን ሰባኪዎች ጋ በመጀመሪያ በከረን ከዚያም ባስመራ ቀጠሉ። አፍ የፈቱበትን የትግርኛ ቋንቋ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ፥ በተጨማሪም ዐማርኛ፣ ላቲንኛ፣ ግእዝ፣ ፈረንሳይኛና ጣሊያንኛ ተምረዋል። ሥነ ሃይማኖትንም አጥንተዋል። በ1900 አካባቢ በኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ቅርንጫፍ የዓለማዊ ካህንነት መዐረግ አግኝተው ስማቸው «አባ ጄሮም» ተብለው ተሰይመዋል። እያስተማሩ፥ አስመራ በሚገኘው የካፑቺን ማተሚያ ቤት ይሠሩ ነበር። በ1918 አካባቢ ከካፑቺኖች ጋራ ተጣልተው ቅስናውንም ኾኖ ኤርትራን ለቀው ወደ ኢትዮጵያ ኼዱ።

እዚያም ላፄ ኀይለ ሥላሴ አገልግሎት መስጠት ጀመሩ። ባዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት እየሠሩ በልዩ ልዩ ምክንያት ብዙ ጊዜ ወደ አውሮፓ ተልከዋል። በተጨማሪም፣ የኢትዮጵያ ነክ አጥኒዎች እንደ ማርሴል ኮኼን፣ ኤንሪኮ ቸሩሊ፣ ማርሴል ግሪዮል፣ እስቴፋን እስትረልሲንና ሌሎችም ኢትዮጵያን በሚጐበኙበት ወቅት ወይም እሳቸው ራሳቸው ወደ አውሮፓ በኼዱ ቍጥር የማያቋርጥ እገዛ አድርገውላቸዋል። ለዳካር-ጅቡቲ ጥናታዊ ጕዞ (1931-1933) የኢትዮጵያ መንግሥት ልዑክ ነበሩ። የኢጣሊያን ወረራ በውስጥ አርበኝነት ስለተቃወሙ፥ በ1941 ያዲስ አበባ ብሔራዊ ቤተ መጻሕፍት የብራና ጽሑፍ ጠባቂ ኾነው ተሾሙ።

ከዚያም በ1965 ጡረታ ከወጡ በኋላ በዦዜፍ ቱቢያና ድጋፍ ወደ ፓሪስ መጥተው እስከ 1977 በኢናልኮ ያማርኛና የትግርኛ ሥነ ጽሑፍ አስተማሪ ኾነው ሠርተዋል።

# JEAN-MAURICE LE GAL

# ዠን ሞሪስ ለ ጋል

(*1938–†2020)



Jean-Maurice Le Gal débute ses études d'amharique à l'École nationale des langues orientales vivantes (ENLOV) en 1965. Parallèlement, il étudie le ge'ez (éthiopien classique) et le sudarabique ancien sous la direction de Monsieur Maxime Rodinson, à la IVe section de l'École pratique des hautes études (EPHE).

Diplômé d'amharique en 1968, il s'initie au tigrigna (sémitique éthiopien septentrional), ainsi qu'à l'agäw et à l'afar (langues couchitiques d'Éthiopie).

En 1970, il est affecté à l'Institut national des langues et civilisations orientales (INaLCO) au titre de Chargé de conférences pour y assurer l'enseignement de l'amharique en suppléance du titulaire de la chaire de la section d'amharique, Monsieur Joseph Tubiana, détaché au CNRS pour deux ans.

Tout en préparant son doctorat en Histoire de la philosophie, Jean-Maurice Le Gal continue à enseigner à l'INaLCO la « Civilisation de l'Éthiopie et des régions adjacentes » sous forme de travaux dirigés et fait des conférences sur « L'histoire des idées philosophiques et religieuses en Éthiopie ».

En 1974, il entre au CNRS comme collaborateur de Monsieur Marcel Cohen. Jean-Maurice Le Gal était l'un des membres actifs de l'Association française pour le développement de la recherche scientifique en Afrique de l'Est (ARESÆ) et du Groupe linguistique d'études chamito-sémitiques (GLECS).

ዠን ሞሪስ ለ ጋል በዘመናዊ የምሥራቅ ቋንቋ ሀገራዊ ትምህርት ቤት (ENLOV)፣ በ1965 ያማርኛ ትምህርት መማር ጀመሩ። ግእዝና ጥንታዊ የደቡብ አረቢያ ቋንቋዎችንም በፕ/ር ማክሲም ሮዳንሶን አማካይነት እከፍተኛ ጥናት ተግባራዊ ተቋም (EPHE) ገብተው ተምረዋል።

ከዚያም በ1968 ባማርኛ ትምህርት ተመርቀው፥ ትግርኛ (የሰሜን ኢትዮጵያ ሴማዊ ቋንቋ) እንዲሁም አገውኛና አፋርኛ (የኢትዮጵያ ኩሽ ቋንቋዎች) አጥንተዋል። በምሥራቅ ቋንቋና ሥልጣኔ ሀገራዊ ተቋም (INalCO/ኢናልኮ) በሚገኘው ያማርኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት ኃላፊ የኾኑት፣ ፕ/ር ዠዜፍ ቱቢያና፣ በ1970 ለሥራ ጉዳይ ወደ ሀገራዊ የሳይንስ ምርምር ማዕከል (CNRS) ሲዛወሩ፥ በሳቸው ምትክ ዠን ሞሪስ ለ ጋል በጊዜያዊ መምህርነት ማዕረግ ተመድበው ለኹለት ዓመታት ያማርኛ ቋንቋ ትምህርት ሰጥተዋል።

ዠን ሞሪስ ለ ጋል ለዶክትሬት ዲግሪ የፍልስፍና ታሪክ ጥናታዊ ጽሑፋቸውን እያዘጋጁ ሳሉ፥ በኢናልኮ « የኢትዮጵያና የጎረቤት አገሮች ሥልጣኔ » የተባለውን የታሪክ ትምህርትና « የፍልስፍናና የሃይማኖት አስተሳሰቦች በኢትዮጵያ » የተሰኘውን ሴሚናር ይሰጡ ነበር።

በ1974 ከማርሴል ኮኼን ጋራ አብሮ ለመሥራት እሀገራዊ የሳይንስ ምርምር ማዕከል (CNRS) ገብተዋል። በተጨማሪም ዠን ሞሪስ ለ ጋል የምሥራቅ አፍሪቃ የሳይንሳዊ ምርምርና ልማት ማኅበር (ARESÆ) እንዲሁም የኩሽና የሴም ቋንቋዎች ጥናታዊ ቡድን (GLECS) አባል ነበሩ።

# MEAZA REVOL-TISSOT

Meaza Revol-Tissot, enseignante-chercheur en tigrigna, a soutenue sa thèse de doctorat « Ètude anthroponymique dans l'aire tigrignaphone : approche comparative des formes guèze et tigrigna » à l'Université Paris III Sorbonne Nouvelle en Langues et civilisations orientales en 1998. Elle a également travaillé comme répétitrice d'amharique à l'INaLCO dès 1974 tout en poursuivant ses études de linguistique.

Ses domaines de recherche portent sur les langues chamito-sémitiques, la philologie et les pratiques langagières dans l'aire tigrignaphone.

Depuis sa retraite en 2014, elle s'intéresse tout particulièrement aux langues couchitiques érythréennes et éthiopiennes et étudie l'arabe et l'hébreu.

# መዓዛ ሬቮል ቲሶ

የትግርኛ መምህርና ተመራማሪ የኾኑት ወ/ሮ መዓዛ ሬቮል ቲሶ፥ በምሥራቅ ቋንቋና ሥልጣኔ ጥናት መስክ « በትግርኛ ተናጋሪ አካባቢ የሰው ስም አሰጣጥ፦ የግእዝና የትግርኛ ስያሜዎች ንጽጽር » የተባለውን የዶክትሬት መመረቂያ ጽሑፋቸውን በፓሪስ III ዩኒቨርሲቲ ሶርቦን ኑቬል አዘጋጁ። የቋንቋ ጥናታቸውን እያካኼዱ ሳሉ፥ ከ1974 ጀምሮ በምሥራቅ ቋንቋና ሥልጣኔ ሀገራዊ ተቋም (ኢናልኮ) ያማርኛ አስተማሪ ኾነው ሠርተዋል።

የምርምር ዘርፎቻቸው የኩሽና የሴም ቋንቋዎች ጥናት፣ ፊሎሎጂና የትግርኛ ቋንቋ አጠቃቀምን ያጠቃልላል። በ2014 ጡረታ ከወጡበት ጊዜ ጀምሮ የጥናት ፍላጎታቸው ኤርትራና ኢትዮጵያ በሚገኙት የኩሽ ቋንቋዎች ላይ ሲኾን በተጨማሪም አረብኛና እብራይስጥ ያጠናሉ።

# RÉFÉRENCES BIBLIOGRAPHIQUES
# ዋቢ መጻሕፍት


Bureau, Jacques. 1997. *Marcel Cohen et ses successeurs*. Addis Abeba : Maison des Études Éthiopienne.

Rouaud, Alain. 1997. *Casimir Mondon-Vidailhet: Pionnier de l'amitie franco-éthiopienne (1847–1910).* Addis Abeba : Maison des Études Éthiopienne.

Rouaud, Alain. 2007. In memoriam Joseph Tubiana (1919-2006). *Aethiopica* 10. 218–220.

Rouaud, Alain. 2020. Un ami de l'Éthiopie : Casimir Mondon-Vidailhet dit Mondon (1847–1910). *Pount* 14.

Rouaud, Alain. 1995. Amharique. In Pierre Labrousse (ed.), *Deux siècles d'histoire de l'École des langues orientales*, 363–369. Paris : Editions Hervas.

Strelcyn, S. 1975. Obituary: Marcel Cohen. *Bulletin of the School of Oriental and African Studies* 38(3). 615–622.

Uhlig, Siegbert & Alessandro Bausi (eds.). 2003–2014. *Encyclopaedia Aethiopica*. 5 Vol. Wiesbaden : Harrassowitz.

Wion, Anaïs. 2009. In memoriam Berhanou Abebe (1932–2008). *Aethiopica* 12. 218–221.

# REMERCIEMENTS
# ምስጋና

Nous remercions chaleureusement Pierre Argaw, Éloi Ficquet, Marc Fontrier, Alain Gascon, Françoise Lair, Jérôme Lentin, Virginie Raimbault, Alain Rouaud et la famille Tubiana de nous avoir fourni des informations indispensables pour rendre hommage aux enseignants présentés dans cette exposition.

ለዚህ ያስተማሪዎች መታሰቢያ ዝግጅት የጐደለውን መረጃ በማሟላት ለረዱን ፒየር አርጋው፣ ኤሏ ፊኬ፣ ማርክ ፎንትሪዬ፣ አለን ጋስኮን፣ ፍራንሷዝ ሌር፣ ዤሮም ላንተን፣ ቪርዢኒ ሬምቦ፣ አላን ሩዎ እና የቱቢያና ቤተሰቦች የልብ ምስጋናችንን እናቀርባለን።